ሳምንታዊ ዜና ዘገባ

ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ራዲዮ የካቲት 21 ቀን 2001 ዓ.ም.

- ወያኔ ትርፍ አምራች እያለ የሸለማቸዉ አርሶ አደሮች የእርዳታ ያለህ እያሉ ጥሪ ማቅረብ መጀመራቸዉ ተጋለጠ፣
- ከ5 ሚሊዮን ህዝብ በላይ አስቸኳይ እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸዉ ወያኔ አመነ፣
- 602 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ያስፈልጋል ሲልም ተማፀነ፣
- ወደ ሱማሊያ ዘምቶ ተመለሰ የተባለዉ ጦር ጥያቄ ማንሳት መጀመሩ ታወቀ፣
- ለተሰዉ ወንድሞቻችን የካሳ ክፍያ ለቤተሰቦቻዉ ይሰጣቸዉ ማለታቸዉ ታወቀ፣
- የወያኔ የጦር ጄኔራሎች እና ካድሬዎች በጦር ጥያቄ ተደናግጠዋል፣
- የልጆቻችንን አይን እንይ ብለዉ ከክፍለ ሀገር ድረስ የመጡ እናቶች ያለ ዉጤት ተመለሱ፣
- መለስ ዜናዊ ከእናንተ ጋር አብሬ አልሰራም ሲል ደኢህዴን ካድሬዎችን አስደነገጣቸዉ፣

የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል።

ዝርዝሩን በሚቀጥለዉ ገፅ ጀምሮ ያንብቡ<<<>>>

በዓመት 11 በመቶ እድገት አስመዘገብኩ እያለ ዲስኩር ሲያሰማ የነበረው የወያኔ ቡድን የእርዳታ ያለህ እያለ ጥሪ ማቅረብ መጀመሩ አነጋጋሪና አስቂኝ መሆኑ ታወቀ::

የወያኔው መሪ መለስን ጨምሮ ሁሉም ባለስልጣናት ባገኙት መድረክ ሁሉ አጥጋቢ ምርት ስለተገኘ ከፍተኛ እድገት አስመዝግበናል እያሉ እየለፈፉ ቢቆዩም ገና የበጋ ወራት ብቅ ሳይል በሀገሪቱ የረሀብተኛ ቁጥር ሊያሻቅብ ስለሆነ ድረሱልን እያሉ መወትወት መጀመራቸው ታውቆዋል::

ወትሮም በውሸት ላይ የተመሰረተው የወያኔ ቡድን ከአፍሪካ በልማት እና በእድገት ግንባር ቀደም ነን እያለ እየለፈፈ ቢሆንም እየታየ ያለው ሀቅ እና እውነታ ግን ፍፁም የተለየ ከመሆኑም በላይ ብዙ እንኩዋን ሳይራመድ በአጭሩ እየተጋለጠ መሆኑ ታውቆዋል::

የወያኔ ቡድን በርሀብ እና በችግር ውስጥ የሆነውን ገበሬ ትርፍ አምራች ነህ እያለ በሀሰት ብረት እያቀለጠ እየሸለመ ቅስቀሳ ቢሰራበትም ያለው እውነታ ግን ከዚህ በተቃራኒ በመሆኑ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ትርፍ አምራች ነው የተባለው አርሶ አደር እንደገና ተርቦዋልና ድረሱለት መባሉ አሳዛኝ ከመሆኑም በላይ አሳፋሪ የወያኔ የተለመደ ቅጥፈት መሆኑን ያሳየ መሆኑን ዘገባው አስረድቶዋል::

በሱማሌ ክልል ውስጥ ለተጎዱ ወገኖቻችን እርዳታ ሲሰጡ የነበሩትን የለጋሽ ድርጅቶች ከተቃዋሚ ኃይሎች ጋር ወግናችሁዋል በሚል ሰንካላ ምክንያት ከሀገር እንዲወጡ ያደረገ ሲሆን የተቀሩትንም ቢሆን እነሱ በያዙት ፕሮግራም መሰረት ለህዝቡ እርዳታ እንዳይሰጡ ለማድረግ እና በህዝብ ላይ የሚሰራው ግፍና በደል እንዳይጋለጥበት በመፈለጉ አሳሪና ገዳቢ ህግ አውጥቶ ከጥቂት ወራት በሁዋላ ተግባራዊ ለማድረግ እየተጣደፈ ባለበት ወቅት 5ሚሊዮን ህዝብ ተርቦዋልና ድረሱልኝ ብሎ ጥሪ ማቅረቡ ትዝብት ላይ የጣለው መሆኑም ታውቆዋል::

የወያኔው ከፍተኛ ባለስልጣን አዲሱ ለገሰ በብቃት ማነስ የተወገደበት ግብርና እና የገጠር ልማት ሚኒስትር መስሪያ ቤት ሰሞኑን ባቀረበው ጥሪ መሰረት 5 ሚሊዮን ህዝብ አስቸኩዋይ እርዳታ ስለሚፈልግ ድረሱልኝ ያለ ሲሆን ይህንን ለመቅረፍ ደግሞ 602 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚያስፈልግም በሰጠው መግለጫ ላይ ይፋ አድርጎዋል::

በባህር ዳር፣ በናዝሬት፣ በአሳይታ፣ በአዋሳ፣በመቀሌ እና በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ ከተለያዩ ወረዳዎች አርሶ አደሮቹን እየሰበሰቡ የቃሊቲ ብረትን አቅልጠው ሜዳሊያ እያሉ ሽልማት ቢያበረክቱም ውሸታቸው ብዙ ርቀት ሳይጉዋዝ እውነታው ተጋልጦ ሊታወቅ የቻለ ከመሆኑም በላይ ገመናቸው አደባባይ ወጥቶ እርቃናቸውን መቅረቱ ታውቆዋል::

የወያኔ አረመኔ ቡድን ሰሞኑን ባቀረበው በዚሁ ጥሪ ላይ አጣዳፊ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው 5 ሚሊዮን ናቸው በማለት በተወሰኑ ክልሎች ብቻ ያሉትን ጠቆመ እንጂ ሁሉም አካባቢዎች ጥናት ቢደረግ ከ7 ሚሊዮን በላይ የሚሆን ህዝብ በከፋ ችግር ውስጥ ሊገኝ ይችላል ሲል የገለፀው የደረሰን ዘገባ እርዳታ አድርጉልኝ በማለት ጥሪ ባቀረበበት ወቅትም ቢሆን በገንዘብ እንጂ በእህል እና በሌላም መልኩ አለመጠየቁ እርዳታ የጠየቀውን ገንዘብ ለተጎዳውና ችግር ለደረሰበት ህዝብ ሳይሆን ለወታደራዊው ተቁዋም  እና ለደህንነቱ መዋቅር ማጠናከሪያ ሊያውለው መሆኑንም ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል።

በየዓመቱ ከፍተኛ አምራች ናቸው በማለት በየክልሎቹ ከተሞች አርሶ አደሮቹን ሰብስቦ የአለምን ህብረተሰብ እና መላው የኢትዮጵያን ህዝብ ለማታለል ሽብ ረብ ለማለት የሞከረው የወያኔ አረመኔ ቡድን በውሸት ደብቆት የነበረው ምስጢር ተጋልጦ ዛሬ መልሶ በአንደበታቸው በካድሬዎቹ አማካኝነት እርዳታ ፈላጊ ያውም አፋጣኝ መኖሩን መግለፁ እሩቅ ሳይሄድ እዚሁ ሊዋረድና እርቃኑን ሊቀር እንደቻለም ዘገባው አስረድቶዋል።

አምና በረሀብ የተጠቃው 12 ሚሊዮን ህዝብ እንደነበረ ለጋሽ ድርጅቶች በይፋ ገልፀው አስቸኩዋይ እርዳታ አለም አቀፉ ማህበረሰብ እርዳታ እንዲሰጥ ሲያሳስቡ የወያኔ ቡድን ግን በሀገሪቱ ምንም ርሀብ እንዳልተከሰተ እና ፍፁም ከነሱ  ቁጥጥር ውጭ የሚወጣ ችግር እንዳልተፈጠረ በማስመሰል ለወራት  ሲደብቁ ቆይተው መጨረሻ ላይ እንደገና ረሀብ መከሰቱን አምነው በረሀብተኛው ቁጥር ላይ ደግሞ ከለጋሽ ድርጅቶች ጋር ሙግት ሲገጥሙ እንደነበር ያስታወሰው የደረሰን ዘገባ ዘንድሮም ተመሳሳይ ቅሌት ይደርስብናል በሚል አስቀድመው የድረሱልን ጥሪ ማቅረባቸውም ታውቆዋል።

ወያኔ ህዝብ እየተራብ እና እየታረዘ በሱማሊያ ሰላም አሰፍናለሁ በሚል በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እያፈሰሰ ያለ አንዳች ውጤት የተመለሰ ሲሆን እዚህ ሀገር ውስጥ ግን በወቅቱ መዳን የሚገባቸው በርካታ ቁጥር ያላቸው ዜጎች ህይወታቸው ሊያልፍ እንደቻለ የሚዘነጋ አይደለም።

የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስትር የነበረው አዲሱ ለገሰ የተባለው ሆድ አደር በብቃት ማነስ ከሚኒስትርነቱ ከተነሳ በሁዋላ መስሪያ ቤቱን በአዲስ መልክ አደራጀን በሚል ቀድሞ እራሱን ችሎ ሲንቀሳቀስ የነበረው የአደጋ መከላከል እና ዝግጁነት ስልጣኑን አሳንሰው አደጋ መከላከል እና ዝግጁነት ኤጀንሲ በሚል በዚሁ መስሪያ ቤት ስር አድርገው እየተንቀሳቀሱ መሆኑን በይፋ የገለፁት የወያኔ ባለስልጣናት የእርዳታ ገንዘቡም ቀጥታ ወደ መንግስት  ካዝና እንዲገባ ለማድረግም ዝግጅቱ መጠናቀቁንም የደረሰን ዘገባ ጨምሮ አስረድቶዋል።

የለጋሽ ድርጅቶች በሀገሪቱ እንደልብ ተንቀሳቅሰው እንዳይሰሩ አስገድዶ ከሀገር የሚያስወጣ ህግ አውጥቶ ዛሬ ችግሩ ሲከሰት የድረሱልኝ ጥሪ ከማቅረቡም በላይ ከለጋሽ ድርጅቶች ጋር እጅና ጉዋንት ሆኜ ለመስራት ዝግጁ ነኝ እያለ ወያኔ መወትወቱ በእጅጉ አስገራሚና አሳዛኝ ነው:: ለተቸገረው ህዝብ እርዳታ እናድርግ ብለው ወደ ሀገር ውስጥ የገቡትን ለጋሽ ድርጅቶች ከማበረታታት ይልቅ ቅስማቸው እንዲሰበር ብርቱ ጥረት ከማድረጉም በላይ በዓለም ላይ ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ ህግ አውጥቶ ካፀደቀ በሁዋላ መልሶ በእነሱ እግር ስር ተንበርክኮ እርዳታ መጠየቁ እጅግ አሳፋሪ መሆኑም ታውቆዋል::

ከፍተኛ ደመወዝ እንከፍላችሁዋለን በሚል እና የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች እንሰጣችሁዋለን በማለት ከየክፍለ ሀገሩ መልምለው እና አሰልጥነው በቀጠሩዋቸው የሰራዊቱ አባሎች ላይ እያሾፉና እየቀለዱ ያሉት የወያኔ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች እና ካድሬዎች አሁንም በተመሳሳይ ተግባራቸው ቀጥለውበት እንደሚገኙ ታወቀ::

በሱማሊያ ሁለት ዓመት ሲዳክር ቆይቶ ያለምንም ውጤት የተመለሰው የወያኔ ጦር ወደ ሀገሩ በሰላም ተመለሰ በሚል ለማጃጃል እና ለማታለል ከፍተኛ ቁጥር ያለው ገንዘብ ወጪ በማድረግ ድል ያለ ድግስ በመደገስ ነገሌ ቦረና ከተማ አቀባበል አደረግንለት ብለው ሲያቅራሩ የነበረ ቢሆንም የድግሱን እፍታ ከወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ጀምሮ እስከ ዝቅተኛ ካድሬ ድረስ ሲያመነዥኩ ከቆየ በሁዋላ ትራፊውን ሰጥተው በራሱ ስም እየነገዱበት መሆኑን የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

ሁለት ዓመት ሙሉ ቀን በሀሩር ሌት በብርድ ሲጠበስ ሲሞትና ሲደማ የነበረውን ሰራዊት ያለ ምንም አላማ ሲያንከራትቱት ቆይተው በድል ተመለሰ ቢባልም ነገሌ ቦረና ላይ መስዋዕት ለሆኑት የሀውልት መስሪያ የመሰረት ድንጋይ አስቀመጥን በማለት የወያኔ ባለስልጣናት ለማታለል ቢሞክሩም የጦሩ አባላት ግን የሀውልት ክምር ለእኛና ለተሰውት ወንድሞቻችን ትርጉም የለውም ይልቅስ ለሞቱት ወንድሞቻችን ቤተሰቦች ካሳ ይከፈላቸው በሚል ጥያቄ ከማቅረባቸውም በተጨማሪ ለራሳቸውም የማዕረግ እና የበረሀ አበል እንዲከፈላቸው መጠየቃቸው ታውቆዋል::

ይህንን የጦሩን ጥያቄ የፈሩት የወያኔ የጦር አዛዦች ሰሞኑን በተለያዩ ቦታና የጦር ክፍሎች ውስጥ ማስመሰያ ለበታች ሹሞች እና ለጥቂት መኮንኖች የማዕረግ እድገት መስጠታቸው ታውቆዋል::

የምዕራብ ዕዝ የተባለው የወያኔ የጦር ክፍል ከሱማሊያ ለተመለሱ የጦር አባሎች ለበታች ሹሞች ከምክትል አስር አለቃ እስከ ባሻ ድረስ የሰጡዋቸው ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ለሚሰሩ ደግሞ ደጀን ሆነው ሲያገለግሉ ነበር በሚል ለጥቂት መኮንኖች የማዕረግ እድገት እንደተሰጣቸው ተገልፆዋል::

በጦሩ አስገዳጅነት የማዕረግ እድገቱ መሰጠት የተጀመረ ቢሆንም ውሉ ላልታወቀ አላማ መስዋዕትነት ሲከፍል የቆየውን ጦር ያላስደሰተ ከመሆኑም ሌላ በከተማ ለነጄኔራል ሳሞራ የኑስ ኪስ መደለብ ከፍተኛ ስራ ሲሰሩ ለነበሩት ጥቂት መኮንኖች የሁዋላ ደጀን በሚል ማዕረግ እድገት መሰጠቱ ቀድሞ በሌላ ምክንያት ቁጣውን ሲገልፅ የነበረው ጦር አሁን ደግሞ የበለጠ ቁጣው እንዲጋጋል ማድረጋቸውን የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል።

የጦሩ ስሜት መቀየርን የተገነዘቡት የወያኔ ሆድ አደር ጦር አዛዥ ነን የሚሉ ያልተማሩት እነሳሞራ የኑስ ጦሩ አሁን ለእረፍት ወደ የቤተሰቡ ቢሄድ ችግር ሊፈጥር ይችላል ከሚል ስጋት እና ፍራቻ ፍቃድ እንዳይሰጣቸው ከመደረጉም በተጨማሪ ሁሉም ወደ ተለያዩ ቦታዎች ተበታትነው እንዲቀመጡ መደረጉንም ዘገባው ጨምሮ አብራርቶዋል።

ብስል ከጥሬ እያማረጡ ጮማ በውስኪ እያወራረዱ በየቅምጦቻቸው መሸታ ቤት እየተመነሸነሹ ያሉት የወያኔ ጄኔራል መኮንኖች ምንም በማይመለከተው የሱማሊያ ጦርነት ህይወቱን ገብሮ ደሙን አፍስሶ በመጣው ጦር ላይ እየተሳለቁ አሁንም ድረስ ለመሸንገል እያደረጉ ያሉት ተግባር እጅግ አሳዛኝ ከመሆኑም በላይ አሳፋሪ መሆኑን የገለፀው ዘገባ የጦሩ አባላት ሁኔታውን በማወቃቸውና በመረዳታቸው ጄኔራሎቹ መደናገጣቸውንም ዘገባው አስረድቶዋል።

በቅርቡ በአዲስ አበባ እና በሌሎቹም የጦር ክፍሎች ውስጥ ውስጡን ሲብላላ የነበረውን የጦሩን ቁጣ ለማብረድ ይረዳል በሚል የተጀመረው የማዕረግ እድገት ቀጣይ መሆኑን ያመላከተው የደረሰን ዘገባ ምናልባትም ከማዕረግ አሰጣጡ ጎን ለጎን በጦሩ መሀል ይቀሰቅሳሉ የተባሉ ጥቂት የተማሩትን የጦሩ አባሎች ለትምህርት በሚል መርጠው ወደ እስር ቤት ሊከቱዋቸው ይችሉ ይሆናል ሲል ዘገባው ግምቱን አስፍሮዋል።

ወደ ሱማሊያ የዘመተው ጦር መመለሱን የሰሙ በርካታ እናቶች የልጆቻቸውን አይን ለማየት ወደ አዲስ አበባ እየመጡ ቀድሞ የምድር ጦር ዋና መምሪያ በሆነው ግቢ በመገኘት ልጆቻችንን አሳዩን አሊያም ያሉበትን ንገሩን በማለት ቢጠይቁም እነ ጄኔራል ሳሞራ የኑስ ምላሽ ከመንፈጋቸውም ሌላ እዚህ አካባቢ መቆምም ሆነ መቀመጥ ክልክል ነው እያሉ እያባረሩዋቸው እንደነበረም የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል።

ሁለት እና ከዚያም ቀናት በላይ ያለ ምግብና መጠለያ እየተንከራተቱ ልጆቻችን ያሉበት ንገሩን ሲሉ እያለቀሱ የነበሩት እናቶች ከክፍለ ሀገር ድረስ መጥተው ሳያገኙ ዋቸው እና በቂ ምላሽ ሳይሰጣቸው በመጡበት አኩዋሁዋን ለመመለስ እንደቻሉ ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል።

በተለይ አንዳንዶቹ እናቶች በሱማሊያ ብዙ ልጆች መሞታቸውን ሰምተናል ስለዚህ እዚሁ ቁርጣችንን ንገሩን እና እንሄዳለን እንጂ ከዚህ ንቅንቅ አንልም በማለት አካባቢውን በለቅሶ ሲያተራምሱት የተመለከተው የግቢው አዛዥ ሌ/ጄ/ል ታደሰ ወረደ በወታደራዊ ፖሊሶች በግዳጅ እየተገፈተሩ እንዲባረሩ ማድረጉን ዘገባው አብራርቶዋል::

በሌላ በኩል ከየጦር ክፍሎች ውስጥ በችሎታና በትምህርት ሳይሆን ለስርዓቱ እና ለአዛዦች ቅርበት ያላቸው መኮንኖች ተመርጠው በጦላይ የጦር ማሰልጠኛ ወታደራዊ ካምፕ ውስጥ ለ6 ወራት የአዛዥነት ኮርስ ሲከታተሉ የነበሩት መኮንኖች መመረቃቸው ታወቀ::

በወያኔው ጦር አዛዥ ታደሰ ወረደ የተመረቁት እነዚሁ ለስርዓቱ ቀኝ እጅ ናቸው ተብለው የመጡት መኮንኖች በስልጠናው ላይ የአዛዥነት ብቻ ሳይሆን የደህንነት ስራ እንዲሰሩ እና ጦሩን አንዳችም የመብት ጥያቄ እንዳይጠይቅ ለማድረግ እርስ በርሱ አቆላልፈው አንገቱን አስደፍተው እንደልባቸው ለማድረግ የሚያስችላቸውን ሁሉ ትምህርት ሲሰጣቸው እንደነበረም የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

በህወሀት 34ኛ ዓመት በዓል ላይ በብሔራዊ ቲአትር አዳራሽ ውስጥ በተከበረው ስነስርዓት ላይ የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት ከፍተኛ ተቃውሞ እንዳጋጠማቸው ተጋለጠ::

ቅዳሜ የካቲት 14 ቀን 2001 ዓ .ም. በብሔራዊ ቲአትር አዳራሽ ውስጥ በአዲስ አበባ የህወሀት ወጣት አባሎች እና አታክልቲ በተባለው በወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣን መሀከል ውይይት የተካሄደ ቢሆንም ውይይቱ ወያኔዎች እንዳሰቡት ሳይሳካ እንደቀረ ለማወቅ ተችሎዋል::

በዚሁ ውይይት ላይ ወጣቶቹ የወያኔውን ባለስልጣን በጥያቄ ያጣደፉት ከመሆኑም በላይ ተቃውሞአቸውን በጭብጨባ እና በፉጨት ሲገልፁ ተደምጦዋል::

ችግር ሲደርስባችሁ ብቻ እኛን ታጋፍጣላችሁ ሌላ ጊዜ ዞር ብላችሁ አታዩንም፤የትግራይ ህዝብን እረስታችሁታል፤ደርግን ለመጣል ስልጣን የያዛችሁት ወያኔ አባላት በሙሉ ከደርግ አምባገነን ስርዓት ባለስልጣናት አትለዩም የሚሉና ሌሎችም ጥያቄዎችን እና አስተያየቶቻቸውን ያቀረቡ ሲሆን መድረኩን ሲመራ የነበረው አታክልቲ የተባለው በለስልጣን እና ሌሎችም የወጣቶቹን ሀሳብ በተልካሻ ምክንያት ለማጨናገፍ ቢሞክሩም ወጣቶቹ በጭብጨባ እና በፉጨት ምላሻቸውን እያጣጣሉ በመጨረሻም ሳይግባቡ ውይይቱ እንደተጠናቀቀ ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል::

ወያኔ ጭቁን የትግራይ ህዝብን ከተቀረው የሀገሪቱ ህዝቦች ጋር ለማጋጨት ብዙ ሙከራዎችን ሲያደርግ የነበረ ቢሆንም በህዝቡ አርቆ አስተዋይነት ሊሳካለት ያልቻለ

ቢሆንም አሁን ደግሞ በወጣቶች በኩል ዘመቻ የጀመረ ቢሆንም በዚህም ሳይሳካለት እንደቀረ ዘገባው አብራርቶዋል።

ጥቂት የትግራይ ተወላጅ ወጣቶችን ብቻ በመመልመል ለወያኔ መጠቀሚያ ለማድረግ ከአንድም ሁለት ጊዜ የተለየ ተልዕኮ ሰጥቶዋቸው ሳይሳካቸው በመቅረቱ እና ወጣቶቹም ድርጊቱን ወደ ሁዋላ መለስ ብለው ሲመለከቱ የወያኔ ሴራና ተንኮል ስለገባቸው ፊታቸውን አዙረው እንደገና በወያኔ ላይ ተቃውሞ ማቅረብ መጀመራቸው ያስደነገጣቸው የወያኔ ባለስልጣናት በጥቅማ ጥቅም ለመደለል እየሞከሩ ቢሆንም እስከ አሁን እንዳልተሳካላቸው ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል።

ወያኔ የከሰረና የወደቀ ፖለቲካውን በህዝቦች ዘንድ ትርምስ በመፍጠር የስልጣን እድሜውን ለማራዘም እየተፍጨረጨረ ቢሞክርም አልሳካ ስላለው ብቻ እንደገና ወጣቶቹን በየብሄራቸው እየከፋፈለ አንዱን ከአንደኛው ጋር ለማጋጨት ውስጥ ውስጡን ሙከራ ቢያደርግም በወጣቶቹ በሳል ትዕግስት ሊኮላሽበት እንደቻለ ዘገባው አስረድቶዋል።

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ እንደፈለገ የሚያሽከረክራቸውን የደኢህዴን ለተባለው የወያኔ ክንፍ ካድሬዎች ሰሞኑን አዲስ መመሪያና ትዕዛዝ ሰጥቶ እያመሳቸው መሆኑን ከአዋሳ የደረሰን ዘገባ ገለፀ።

ከአዋሳ የደረሰን ዘገባ እንደገለፀው ከሆነ መለስ ዜናዊ የደኢህዴን ካድሬዎችን ለማስጠንቀቅ የቻለው ከዚህ ቀደም በወላይታ ሶዶ ከተማ የድርጅቱ 5ኛ ጉባኤ በተካሄደበት ወቅት የተማሩት የደኢህዴን ካድሬዎች አንድ ሰው እስከ መቼ ድረስ ባለበት ስልጣን ይቀጥላል? ለምን የጊዜ ገደብ አልተቀመጠም? ለምንስ ከአንድ ፓርቲ ብቻ ሊመረጥ ቻለ? እስከመቼ በዚህ አይነት እንቀጥላለን? የሚሉ ጠጣር ጥያቄዎችን ለፓርቲው መሪ ለኃይለማሪያም ደሳለኝ ያቀረቡ ቢሆንም ምንም አጥጋቢ መልስ ባለማግኘታቸው ጥያቄው በካድሬዎቹ ዘንድ እየሰፋና እየገዘፈ በመምጣቱ መሆኑን የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል።

በዚህም የተነሳ የደኢህዴን ፓርቲ ለሁለት የተከፈለ ሲሆን እነ ኃይለማሪያም ደሳለኝ ለወያነው መሪ መለስ የወገኑ ሲሆን ሌላው ወገን ደግሞ ጥያቄ ሲጠይቁና እስከ አሁን ድረስ መልስ ያላገኙት ብዙሀኑ ካድሬዎች አንድ ላይ በመሆን በቃላት እየተፋለሙ መሆኑንም የደረሰን ዘገባ ጨምሮ አስረድቶዋል።

በደኢህዴን 5ኛ ጉባኤ ላይ የተነሱት ጥያቄዎች ምላሽ ሳያገኙ የኢህአዴግ 7ኛ ጠቅላላ ጉባኤ በአዋሳ በተደረገበት ወቅትም ተመሳሳይ ሁኔታ ተከስቶ እልባት ሳይገኝ መቅረቱን ያስታወሰው የደረሰን ዘገባ ችግሩ እየሰፋና እየተለቀ ከመሄዱም በላይ ለነመለስ የእግር እሳት ስለሆነባቸው ካድሬዎቹን ሰበብ እየፈለጉ ለማባረር እና ወደ እስር ቤት

ለመክተት የተለያዩ ምክንያቶችን ቢጠቀሙም ሳይሳካላቸው በመቅረቱ ሰሞኑን አዲስ ስልት ይዞ ብቅ ማለቱ ታውቆዋል፡፡

በዚህም መሰረት የወያኔው መሪ መለስ እነዚህን ቡድን መስርተው የተደራጁትን የሻእቢያና የተቃዋሚ ኃይሎች አመለካከት ያላቸው ካድሬዎች ጥያቄያቸውን ካላነሱ ወይም ከቦታቸው ላይ ካልተወገዱ በሚቀጥለው 2002 ምርጫ አብሬ ከደኢህዴን ጋር ለመሳተፍ አልችልም፡፡ ደኢህዴንም ከኢህአዴግ ጋር ተቀላቅሎ መወዳደር አይችልም በማለት ለኃይለማሪያም ደሳለኝ እና ሌላ ለጊዜው አንድ ስሙ ያልታወቀ ባለስልጣን ማስጠንቀቂያ የሰጣቸው ሲሆን የመለስን ትዕዛዝ ተቀብለው አዋሳ በመሄድ ተግባራዊ ለማድረግ የደኢህዴን ካድሬዎችንና ቁልፍ የክልሉ ባለስልጣናትን ስብሰባ ጠርተው ለማሳመን ቢሞክሩም ሳይሳካላቸው እንደቀረ የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል፡፡

የመለስን ቃል ለማስከበር ወደ አዋሳ የሄዱት ሁለቱ የወያኔ ባለስልጣናት ስብሰባ ጠርተው ለማሳመን ቢሞክሩም ከክልሉ ፕሬዝዳንት ሽፈራው ሽጉጤ ጀምሮ ሌሎችም ካድሬዎች እነዚህን ለማባረር እና እርምጃ ለመውሰድ የእኛ ስልጣን ሳይሆን የጠቅላላ ጉባኤው ስለሆነ አሁን መወሰን አንችልም ሲሉም ምላሽ የሰጡ መሆናቸውንም ዘገባው አብራርቶዋል፡፡

እነ ኃይለማሪያም የመለስን ትዕዛዝ ይዘው አዋሳ ድረስ ሄደው ያለውጤት የተመለሱ ቢሆንም መለስ ዜናዊ አዲስ ስልት እና ዘዴ በቅርቡ ቀይሶ ከምርጫው በፊት ሊያጠቃቸው እንደሚችል ዘገባው አስረድቶዋል፡፡

መለስ ዜናዊ በሚቀጥለው ምርጫ አብሬ ከናንተ ጋር አልሳተፍም ብሎ ቁጣና ማስፈራሪያ የሰጣቸው የደኢህዴን ካድሬና ባለስልጣናት ከወዲሁ እራሳቸውን ለምርጫ ለማዘጋጀት ሲሉ አዲስ ዘመቻ መጀመራቸውም ታውቆዋል፡፡

በመሆኑም በአዋሳ ፤በአርባ ምንጭ ፤ በዲላ፤ በወላይታ ሶዶ እና በሌሎችም የክልሉ ከተሞች ውስጥ ካሉ ትምህርት ቤቶች መምህራኖች እና ተማሪዎች መካከል ተመርጠው ለስርዓቱ ቅርበት አላቸው የተባሉትን ለምርጫ ዘመቻው ቅስቀሳ እንዲያደርጉ በቀን ብዙ ብር እንደተከፈላቸው እና በአሁኑ ሰዓት ኮርስ እየወሰዱ መሆኑም ታውቆዋል፡፡